# ትላንት ዛሬ አይደለም

ከፀሃዩ ደባልቀው
ዋሽንግተን ዲ.ሲ.

አሁንለታ ሬዲዮ ስጉረጉር ድንገት ስግብግብ አለና ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ ያለው ቃለ-መጠይቅ ትኩረቴን እዚያው ሙሉ በሙሉ ሠረቀና አስቀረው:: ብዙ ነገር ተባለና ግን ከዚያ ቃለ መልልስ ውስጥ በአእምሮዬ ተቀርፆ የቀረ አባባል ይሞግተኝ ገባ:: ነገሩ እንዲህ ነው፣ አቶ አንዳርጋቸው፣ ወይም ሌላ የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አባል ወደ አሥመራ ያቀና ነበር ወይ? ስሞኑን ጉምጉምታ፣ ጭምጭምታ፣ እየተሰማ ነበር:: እረ እንዲያውም ባንዳንድ ድረ-ገፆች ፍርፍርጥ ብሎ የቀረበበት ሁኔታም አለ:: አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ፀሐፊ ከሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ተገናኝተው መከሩ የሚል ይልና የኘሮግራሙ አቅራቢ የእለቱ እንግዳ ሆነው ለቀረቡት ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪ ጥያቄውን ወርወረላቸውና እስቲ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሉትን ይበሉ በማለት መድረኩን በርግዶ ለቀቀላቸው:: ዶ/ር ብርሃኑም ሲመልሱ እርግጠኛ ነኝ ቃል በቃል አልያዝኩትም:: ጭብጥና ይዘቱ ግን አሁንም ፍንትው ብሎ ይታወሰኛል:: «በኢትዮጵያ ጉዳይ አንደራደርም ምክንያቱም ሥልጣኑም መብቱም የኛ አይደለም:: ውክልናም የለንም:: በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ መነጋገር የሚችለው የሥልጣኑና የመብቱ ባለጉዳይና ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻና ሕዝቡ በነፃ ፈቃዱ ይሁንታውን ሰጥቶ ውክልናውንና አደራውን የሚያስረክበው የሕዝቡ ተወካይ ብቻ ነው:: በማለት ይመልሱና ሰውዮው ሄደው ነበርን ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ነው በማለት ቅጭም ይላሉ አሁንም ጠያቂው የተሰጠው ጠሊቅ ፈላስፋዊና ሊቀ-ሊቃውንታዊ ምሁራዊ ስንክሳር እንዳልገባውና ላቀረበው ጥያቄ እንደመልስ ለመቀበል እንዳልዳዳው ለማሳዬት የግንቦት 7 አመራር ወደ ኤርትራ አልሄደም ነው የሚሉኝ አለና አሉታዊ መልስ ከተሰጠው ማስረጃውን ሊዘረግፍባቸው እቋፍ ላይ እንደደረሰ በሚያመለክት ቆንጣጭ ድምፀት ወጠራቸው:: አልሄድንም እንጂ ብንሄድ የትግል ስልታችን ምን ይሁን ምን እግባችን የሚያደርሰንን መንገድ ስለምንከትልበት አኳኋን ከቶውኑ ስለያንዳንዱ የትግላችን አሰነዛዘር የወያኔን ፈቃድ እየጠየቅን ወይንም በአደባባይ እንዳሁኑ በሬዲዮ እየለፈፍን የምንሄድበት ጉዳይ አይደለም:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠቅማል ብለን እስካሰብንና እስካመነን ድረስና ወዳስቀመጥነው ግብ ይወስደናል ብለን እስካመንን ድረስ የትግል ስልታችን በሰላማዊ ይሁን በትጥቃዊ ወይም ሁለቱንም መንታ መንገዶች መጠቀም ካስፈለገ የኛና የኛ ውሳኔ ብቻ ነው ሲሉ አረፋት::

ምኑን ልጨብጠው የሚል በሚመስል ቅላፄ «እና ሄደቹሃል ማለት ነው » ሲል አሁንም ለአማርኛው ያማርኛ ፍቺ እንዲሰጡት የመወትወት ዓይነት ግፊት አደረገባቸው:: አልኩህ እኮ እኛ የትም ብንሄድም ወደ አሥመራ ብንጓዝም በኢትዮጵያ ጉዳይ የመደራደር ሥልጣኑም መብቱም ውክልናውም የለንም:: የሕዝቡ ነውና ኋላ ላይ አሉ እኛ የመረጥነውን የትግል ስልት ተጠቅመን ሥልጣን ላይ ስንወጣ ያኔ ሕዝቡ በፈቃደኝነትና በነፃ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ውክልና ሲሰጠን በሀገር ጉዳይ ላይ መደራደር እንችላለን አሉና ፍርጥም ብለው አሁንም ሊህቃዊ እስጥ አገባቸውን አስከተሉበት በእርግጥ አሉ ዶ/ር ብርሃኑ በማያያዝ ወያኔ በአሁኑ ጊዜ የግንቦት 7 ንቅናቄን ለማዳከም ባለው እኩይ መነሻ አባላቶቻችንን እያሳደደና እያዋከበብን ስለሆነ ሸሽተው ድንበር ተሻግረው መጠለያና መሸሸጊያ ፍለጋ ወደ ኤርትራ የዘለቁ አያሌ አባሎቶቻችን እዚያው ይገኛሉ:: እናም የእነዚህን አባላት ጥገኝነትና አያያዝ ምን ይሁን በሚለው ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ከሻዕቢያ መሪዎች ጋር እየመከርንበት ነው አሉ:: በስልክ፣ በጽሁፍ፣ በስማ በለው፣ በሦስተኛ ወገን፣ ወይም እዚያው በግንባር በአካል ተገኝተው ይሁን አይሁን ፍንጭ ሳይሰጡ ሙልጭልጭ ብለው ለማምለጥ ሞከሩ::

እኔም የዶ/ር ብርሃኑ ምላሽ ዱብልብል እያለ ስላስቸገረኝ እስካሁን የሰማሁትን ወደማስላሰሉ አዘገምሁ:: እናም በሚከተለው ሁኔታ ጉዳዩ የገባኝ መሰለኝና ሃሳቤን ላክፍላችሁ ፈቀድሁ::

ዶ/ር ብርሃኑ በፈለግነው የትግል ስልት መጠቀም የኛው ሥልጣን ነው የሚሉት እውነት ነው :: የሳቸውና የግንቦት 7 ንቅናቄ እምነት በአመፅና በሽብር ኢትዮጵያን መናጥ ነው:: ይህ የምርጫ ጉዳይ ከሆነ ምርጫው እርግጥም የነዶ/ር ብርሃኑ እንጂ በምሁራዊ ድምፀት እንዳመኑት የምልዓተ ሕዝቡና የብሔር ብሔረሰቦች ምርጫ አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ምርጫ የአመፅ መንገድን ክርችም አድርጎ የዘጋ የሰላምና የዲሞክራሲያዊ የትግል አግባብን ብቻ በይሁንታ በይፋ ያወጃ አካሄድ ነው:: ይኸንን የሕዝብ የሉአላዊነት መገለጫ የሆነውን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በአመፅ የመናድ ጉዳይን በሚመለከት እነ ዶ/ር ብርሃኑ መርጠነዋል በሚሉት የትግል ስልት መሆኑ ነው ከሻዕቢያ መሪዎች ጋር አባሎቻቸው ስልጥነውና ታጥቀው፣ በሻዕቢያ አንቀልባ ታዝለው ለሽብር ተግባር ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደሚሸጋገሩ «ስለ አባሎቻቸው ጥገኝነትና አያያዝ» እንደተነጋገሩ እሳቸውም አልደበቁም ታዲያ! ሕዝቡ የመረጠውን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ አሽቀንጥረው ወዲያ በማለት የጥፋትና የሽብር መንገድን እንዲጭኑበት እንዲያስፈፅሙለት እውን ውክልናውን ሰጥቶቻቸዋልን? ለዘመናት እርስ በርስ ሲያናቁሩንና ሲያፋጁን የነበሩትን አድሎአዊ ሥርዓቶች በትግላችን

አስወግደን ዛሬ የሰላም አየር እየተነፈስን፣ ፍትሃዊ አንድነታችንን በዲሞክራሲያዊ አግባብ በሂደት እናረጋግጣለን ብሎ በሙሉ ልብ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰላም ማወክ ብሔራዊ ጉዳይ ሆኖ የራሱን ብሔራዊ አጀንዳ ለድርድር ማቅረብ ነው ካልተባለ ዶ/ር ብርሃኑ የሚሰጠት ፍቺ ሊሆን የሚችለው «ንቀት» ብቻ ነው:: የተለመደው እኛ እናውቅልሀለን የሚል የግብዞች ፈሊጥ ነው:: መመጻደቅና እልፍ ሲልም ተጨፈንና እናሞኝህ እንደ ማለት ነው::

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ርቆት የነበረውን ልማት በቁርጠኝነት ተያይዞታል:: በመሆኑም የዓለም የኢኮኖሚ ጠበብትና ተቋማት የሚሰጡትን አዎንታዊ ምስካሬ ለትግሉ መቀጠል ዓይነተኛ ግፊትና ስንቅ ቢሆነውም ከዚያ በላይ ግን በዓይኑ በብረቱ የሚያያቸው፣ የሚዳሰሱትና የሚጨበጡት የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ለውጦች የራሱ ቁጭትና ጽናት መገላጫ ውጤቶች እንደሆኑ በእለት ተእለት ሕይወቱ በማጣጣም ወደፊት እየገሠገሠ ነው:: ትላንት በሀገሪቱ ለመድኃኒትነት ያህል ሁለት ዩኒቨርስቲዎች የነበሩበት ሁናቴ ተቀይሮ ዛሬ 23 ዩኒቨርስቲዎች ለ200 ሺህ ያህል ተማሪዎች የእውቀት ገበታ እያቀረቡ ይገኛሉ:: ከአንድና ሁለት ዓመታት በኋላም አሁን በመገንባት ላይ ያሉት የ10 ተጨማሪ ዩኒቨርስቲዎች በሮች ወለል ብለው ሲከፈቱ በሀገራችን በሃያ አመታት ውስጥ 31 ዩኒቨርስቲዎች ተገንብተው ከነባሮቹ ጋር 33 ዩኒቨርስቲዎች ይኖሩናል ማለት ነው::

ይህ ተአምራዊ የልማት ውጤት የሕዝብ ምርጫ በሆነው ሰላማዊ ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ ንፍቀ ክበብ ውስጥ ሕገ መንግሥታዊና ፌዴራላዊ ሥርዓት የመገንባቱ ሂደት ውጤት ነው:: በሁሉም መስክ ዛሬ በሀገራችን በጠቅላላው ወደ አንድ መቶ ቢሊዮን ዶላር የኢንቨስትመንት ፍሰት አለ:: ይህ አሃዝ የመንግሥትን የልማት በጀት አይጨምርም:: መዋዕለ ንዋዩ በግል ኢንቨስተሮች በመላው ሃገሪቱ የዋለ አንጡራ ሃብት እንደመሆኑ በመቶ ሺዎች የተቆጠሩ ዜጎች ሥራ እንዲያገኙ ሰፊ እድል የከፈተ ብቻ ሳይሆን በዓይነቱም አዲስ ነው:: በሀገራችን ከ18 ዓመታት በፊት ሰፍኖ የነበረው የማዕከላዊ ኘላን ሶሻሊስታዊ ኢኮኖሚ የግል ኢንቨስትመንትን የሚያደፋፍር አልነበረምና፣ ከዚያ ወዲህ ለአብነት ያህል በመላ ሀገራችን የናኙት ከ10 በላይ የሆኑ የግል ባንኮችን ማንሳቱ ይበቃል:: በተጨማሪ በውጭ እርዳታና ልገሣ እንዲሁም በአመዛኙ በመንግሥት በጀት በመገንባት ላይ ያለት የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኘሮጀክቶች፣ መንገዶችና ድልድዮች የከተማ ነዋሪዎች ሕንፃዎች የተየሌለ ናቸው:: እነኚህ የልማት ተሰፋ ሰጭ ጅማሮዎች ሊረጋገጡ የቻሉት ሀገራችን ኢትዮጲያና ሕዝቦቿ የሰላም አየር ለመተንፈስ ሁነኛና አስተማማኝ እፎይታና ፋታ በማግኘታቸው ነው:: ይህ ለዘመናት

የዘለቀው የርስ በርስ ጦርነት፣ መናናቅ፣ በጉሪጥ መተያየትና መናከስ ቆሞ ሕዝቡ ቀልቡን ሙሉ በሙሉ ለልማት፣ አቅሙንና ጉልበቱን እንዲሁም እውቀቱን ድህነትን ለአንዴንና ለሁሌም ጠራርጐ ለመቅበር በጽናትና በቁርጠኝነት በሕብረት በቃኝ ብሎ ሆ ብሎ በመነሳሳቱ ነው፡፡

ታዲያ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪዎች በኤርትራ መሪ ጉያ ሥር ለመወሸቅ ሽር ጉድ የሚሉት የኢትዮጵያን ሕዝብ የተረጋጋ ሰላም ልማትና ዲሞክራሲያዊ ሂደት በእንጭጩ ለማኰላሸት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ፋይዳ ሊያመጡለት ነው ?

ይህ የተደገሰለት ሴራ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ከጠላት ጋር መደራደር ካልተባለ ሌላ በምን ምሁራዊ ስላቅና ምፀት ይገለጽ ይሆንን ? ዶ/ር ብርሃኑ ግንቦት 7 ከሻዕቢያ ጋር የሃገር ጉዳይን አስመልክቶ ለድርድር አያቅርብም ሲሉ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሀገር ጉዳይ ማለት እኮ ሕዝቡ ድህነትን ሙሉ በሙሉ በማስወገድ ኢትዮጳያ ከሃያ ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ከዓለም የመካከለኛ ገቢ ሃገራት ሰልፍ ውስጥ እንድትገባ በጽናትና በቁርጠኝነት የሚያደርገው እልህ አስጨራሽ ትግል ነው፡፡ ዛሬ የሀገር ጉዳይ ማለት የኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ ብሔርና ብሔረሰቦች ፍትህንና መልካም አስተዳደርን በማረጋገጥ በመካከላቸው ፍትሃዊና ርትአዊ የአንድነትና የጥንካሬ መንፈስ ዳብሮ በሕዝቦቿ እኩልነት ልማቷ የተፈጠነና ሥልጡን ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን የተላበሰች ዘመናዊትና አዲሲቷን ኢትዮጵያን በአዲስ መዳላድል የማወቀር ትግል ነው፡፡ ዛሬ የሀገር ጉዳይ ማለት እኮ ሕዝቦቿ ድንበርና ክልል ሳይገድባቸው ያላቸውን የመዋእለ ንዋይ ጥሪት እውቀትና ጉልበት በአመቻቸው መንገድ በመረጡት ቦታ የሚያፈሱባት ሁሉም ሕዝቦች በየደረጃው የፈጣን ልማቷ ትሩፋት ባይተዋር ሳይሆኑ ተቋዳሽ የሚሆኑባትን አዲስቱን ኢትዮጳያን፣ በሕዝቦቿ ፍቅርና የአንድነት ስሜት የተሳሳረች ጠንካራ ሃገር እውን ማድረግ ነው፡፡ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሀገር ጉዳይ ማለት እኮ በሕዝቦቿ ፍትሃዊ አንድነት ላይ የተገነባ ወጥ ኢትዮጵያዊነት በሕብረ-ብሔራዊት ኢትዮጵያ ፋፍቶና ደምቆ የሚንፀባረቅባት ታፋራና ተከብራ ከጉረቤቶችዋና ከሌላው ዓለም በእኩልነት በመግባባትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን በሰላማዊ ትብብር አረጋግጣ የምትታይ የበለፀገች ኢትዮጵያን መቅረጽ ነው፡፡

ዛሬ የሀገር ጉዳይ ማለት ግዑዝ ነገር አይደለም፡፡ ሕዝቦችና ብሔር-ብሔረሰቦች በሁለንተናዊው ፋይዳ ቀጥተኛ ተዋናይ፣ የበይ ተመልካች ሳይሆኑ የጥቅሟ ፍትሃዊ ተቋዳሽ የህልውናዋ ንቁና አስተማማኝ ዋስትና የሆኑባት የትላንት ትውልዶች ያስረከቡንን አምንታዊ ታሪካዊ ባህላዊ ተፈጥሮአዊና መንፈሳዊ የሀገር ፍቅር

የአርበኝነትና የነፃነት እሴቶችን ጠብቀንና በአዲስ የፍትህ፣ የሰላም የልማት የሰብአዊ መብት፣ የእኩልነት፣ የርትእና የዲሞክራሲ ፈርጦች አዳጉሰንና ይበልጥ አበልፅገን እጅ ለእጅ ተያይዘን በኅብረት የምንጓዝበት አዲሲቷን ኢትዮጵያን ማረጋገጥ ነው።

በመሆኑም የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ትላንት ከትቢያ የተነሱት የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ናቸው ሲለን ግንቦት 7 ደግሞ ይሕንን አንቀበልም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሽብር በሁከትና ብጥብጥ እናናውጠዋለን ይለናል። እናም ኤርትራ ሄደን በሃገር ጉዳይ ላይ መደራደር የለም ሲሉን ለመመለስ የምንመኘው ግን የሻዕቢያን ስንቅና ትጥቅ ተሸልመን ከቻልን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትህን ንደን፣ ሰላምህን አደፍርሰን፣ ልማትህን አስተጓጉለን፣ ነፃ ልናወጣህና እኛም በአቋራጭ ሥልጣን ላይ ለመውጣት ነው ማለታቸው አይደለምን! ለዚህ ደግሞ የኢትዮጲያ ሕዝብ ምላሽ «እንቁራሪት በሕልሟ ዝሆንን አክላ » አደረች በማለት በሉ ይህ እኮ የምናውቀው የወለፈንዴ ባህርይ ነው ይላቸውና ለህገ መንግሥታዊና ለፌዴራላዊ ሥርዓቱ ምስጋና ይግባውና ዛሬ በመላው ሀገራችን 15 ሚሊዮን ተማሪዎች ከእውቀት ማዕድ ለመቋደስ በየዕለቱ በት/ቤቶች ይውላሉ። ይህ ማለት ከእያንዱንዱ መቶ ኢትዮጵያውያን መካከል ሃያዎቹ በትምህርት ገበታ ላይ ይውላሉ ማለት ነው። ዘመኑ ተቀይሯል። እናም መጣጥፌን ለመቋጨት በአንድ ወቅት አቀንቃኙ እሳቱ ተሰማ ካንጐራጐረው ዘፈን ሁለት መስመር ሰበዝ ልዋስና ተበድሮም ተለቅቶም እንደ ነገር ማለት ያለ ነውና እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን እያሰበ የተጫወተው ይመስል

«ወደኋላ እየሄድሽ በሃሳብ ከማለም
ቀኑ እንዳይመሽብሽ ትላንት ዛሬ አይደለም»

በሚለው የአርቲስቱ ስንኝ ልሰናበታችሁ።